# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ -ሰመጉ
# HUMAN RIGHTS COUNCIL -HRCO

ታህሳስ 27 ቀን 2010

## ጋዜጣዊ መግለጫ

### የገዢው ፓርቲ (ኢህአዴግ) ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሰጠው መግለጫ ላይ በመመስረት በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ከሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ የተሰጠ መግለጫ

ባለፉት ሁለት ሳምንታት፣የገገርው ፓርቲ ኢሕአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ባካሔደው ስብሰባ፣ በሀገራችን የፖለቲካ ምሕዳር መጥበቡን፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በየቦታው የሚታዩ መሆኑንና ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲዳብር ተገቢው ጥረት በመንግስት አለመደረጉን እንዲሁም በአጠቃላይ አገሪቱ አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ መውደቋን በመገምገም፣ በዚህ ምክንያት በሐገሪቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት የገገርው ፓርቲ አመራር ኃላፊነቱን እንደሚወስድ በመግለጽ ፓርቲው መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል። የግንባሩ አባል ድርጅቶች አመራሮችም ታሕሳስ 25 ቀን 2010 ዓ.ም. በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ይህንኑ በድጋሚ አረጋግጠዋል። በመቀጠልም፣ በግምገማው መሠረት መሰረታዊ የማሻሻያ እርምጃዎች እንደሚወሰዱና፣ ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠርና የዲሞክራሲ ምሕዳሩን ለማስፋት፣ በቅድሚያ በወንጀል ተከስሰው የተፈረደባቸውና ጉዳያቸው በፍርድ ሂደት ላይ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና ሌሎች ግለሰቦች እንደሁኔታው ክሳቸው እንዲቋረጥ ወይም ምሕረት እንዲደረግላቸው በማድረግ ከእስር እንደሚፈቱ እንዲሁም የማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ እንዲዘጋ መወሰኑን፣ የግንባሩ ሊቀመንበር እና የሐገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ገልጸዋል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ነፃና ገለልተኛ የሰብዓዊ መብት ተከላካይ ተቋም እንደመሆኑ መጠን፣ መንግስት የፖለቲካና የሕሊና እስረኞችን ለመፍታት፣ እንዲሁም ከ40 ዓመታት በላይ የዜጎች የሰቆቃና የስቃይ ቦታ ሆኖ የቆየውን የማዕከላዊ ምርመራ ተቋም ለመዝጋት ያሳየው ተነሳሽነት ሊበረታታ የሚገባው መሆኑን ያምናል። በዚህ ረገድ መንግስት በቀናነት፣ ያለአድልዎና የፖለቲካ ትርፍ ስሌት፣ ሁሉንም የሕሊና እና የፖለቲካ እስረኞች ነጻ በማድረግ ለዲሞክራሲና ብሔራዊ መግባባት ያለውን ቁርጠኝነት እንዲያረጋግጥ ሰመጉ አበክሮ ይጠይቃል።

ሰመጉ በየጊዜው በሚቀርቡለት አቤቱታዎች፣ ባካሔዳቸው ምርመራዎችና በችሎት የፍርድ ሂደት ክትትል የደረሰባቸው ግኝቶች፣ የማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ተቋም፣ በዜጎች ላይ አስከፊና ዘግናኝ የጭካኔ እና የማሰቃየት ተግባር እንደሚፈጸምበት፣ ዜጎች ለከፋ የአካል ጉዳት፣ ለማይሽር የአእምሮ ጠባሳና ስነልቡናዊ ጉዳት፣ አልፎ ተርፎም ለሞት የተዳረጉበት መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። ፍርድ ቤቶችም ጭምር በማዕከላዊ ምርመራ የተሠጠ የዕምነት ቃል በድብደባና ስቃይ የተገኘ መሆኑን በማረጋገጥ ሁኔታው በከፋባቸው የተወሰኑ መዝገቦች ተከሳሾች ነጻ እንዲወጡ መወሰናቸው ይታወቃል። ይሁንና በዜጎች ላይ የማሰቃየትና የሰቆቃ ተግባር የሚፈጸመው በማዕከላዊ ብቻ ሳይሆን፣ በበርካታ የፌደራልና የክልል ፖሊስ ጣቢያዎች፣ እንዲሁም የደህንነትና የማረሚያ ቤቶች ወይም የቀጠር እስረኞች ማቆያ ተቋማት በመሆኑ፣ በማዕከላዊም ሆነ በእነዚህ ተቋማት ይህን አስከፊ ወንጀል



የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ Human Rights Council

ሲፈጽሙ የቆዩ መርማሪዎች፣ የፖሊስና የደህንነት አባላት በአስቸኳይ ምርመራቸው ተጣርቶ በህግ እንዲጠየቁ ሰመጉ ያሳስባል። በዚህ ድርጊት ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች ተገቢው ካሳ እንዲከፈል፣ እንዲሁም ወደፊት ይህ እንዳይደገም ሲቪል ማሕበረሰቡ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ እና በፍርድ ቤቶችም ያላሰለሰ ክትትል፣ ቁጥጥርና የዕርምት እርምጃ እንዲወሰድ ሰመጉ ይጠይቃል። በዚህ ረገድ የፌደራል ወንጀል ምርመራ ተቋም አለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንደገና እንዲደራጅ መወሰኑ የሚበረታታ ሲሆን፣ የተቋሙ ስራ ሰመጉን ጨምሮ ለሌሎች የሰብዓዊ መብት ተከላካይ ድርጅቶች ክትትል ክፍት እንዲደረግ፣ በተለይም የወንጀል ምርመራ ስራ በግልጽና በቪዲዮ ካሜራ ዕይታ ስር ጭምር እንዲከናወን በማድረግ መንግስት በዚህ ረገድ ያለውን ቁርጠኝነት ሊያሳይ ይገባል።

ባለፉት 3 ዓመታት በተደረገው ሕዝባዊ ተቃውሞ የመንግስት ጸጥታ ኃይሎች፣ በተለይም የፌደራል ፖሊስና መከላከያ ሰራዊት አባላት፣ በኦሮሚያና አማራ ክልሎች ከመጠን ያለፈና አላስፈላጊ የሐይል እርምጃ በመውሰድ፣ባልታጠቀ ሰላማዊ ሕዝብ ላይ የግድያና የአካል ማቁሰል ድርጊቶች መፈጸማቸውን ሰመጉ ባወጣቸው ሪፖርቶች ገልጿል። ነገር ግን፣ የፌደራል መንግስት ድርጊቱን የፈጸሙ ግለሰቦች ለፍርድ እንዲቀርቡም ሆነ፣ ጥሰቱ እንዲቆም ተጨባጭና ወቅታዊ እርምጃ ሲወስድ አልታየም። ይልቁንም በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በብሔራዊ የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሐግብር ጽ/ቤት ከዓመታት በፊት የተዘጋጀው የሐይል አጠቃቀምና ተጠያቂነት መመሪያ፣ ተገቢው ውይይት ተደርጎበት እንዳይፀድቅ በአንዳንድ የደህንነትና ፖሊስ ኃላፊዎች መሰናክል በመፈጠሩ፣ የዜጎችን ሕይወት ለመታደግና መብታቸውን ለማስጠበቅ ሳይቻል እንደቀረ ሰመጉ መረጃ አለው። በሌላ በኩል፣ በአንዳንድ የክልል የጸጥታ ሃይሎች በተለይ ባለፉት 2 አመታት ዜጎች ሰላማዊ ተቃውሟቸውን በሚያሰሙበት ወቅት መብታቸው በአባላቱ እንዳይጣስ ለወሰዱት ጥንቃቄ፣ እና የሰብአዊ መብት ጥሰት የፈጸሙ የመከላከያ እና ፌደራል ፖሊስ አባላት ለፍርድ እንዲቀርቡ በማድረግ ላሳዩት አርአያነት ያለው ተግባር ሰመጉ ሳያመሰግን አያልፍም።

ሰመጉ ላለፉት 25 ዓመታት ባወጣቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሪፖርቶችና መግለጫዎች፣ የፖለቲካ ምህዳሩ በከፍተኛ ሁኔታ መጥበቡን፣ የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ከጊዜ ወደጊዜ መጨመሩንና፣ ይህም ለሐገሪቱ ህልውና ጭምር አስጊ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገልጽ መቆየቱ አይዘነጋም። የዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቀንን በማስመልከት ታሕሳስ 1 ቀን 2010 ዓ.ም ባወጣው መግለጫም ይህንኑ በአጽንኦት በመግለጽ፣ መንግስት የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት ተገቢ እርምጃዎችን እንዲወስድ፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የፈጸሙ አካላት ለፍርድ እንዲቀርቡና ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎችም እንዲካሱ ተገቢውን ጥረት እንዲያደርግ ጥሪ ማድረጉ ይታዎሳል።

ዘግይቶም ቢሆን፣ መንግስት በዚህ ረገድ ከላይ የተጠቀሱትን እርምጃዎች ለመውሰድ መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም፣ በዘላቂነት ሰብዓዊ መብት ለማስከበርና ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን በሀገሪቱ ለመገንባት፣ መንግስት መሠረታዊ የህግ፣ የተቋምና የአሰራር ማሻሻያዎችን ማድረግ እንዳለበት ሰመጉ አጥብቆ ያምናል። በመሆኑም፣ የፖለቲካ ምሕዳሩን ላለፉት በርካታ ዓመታት ያጠበቡትን የፀረ ሽብር ፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት እንዲሁም የምርጫና የመገናኛ ብዙሃን ሕጎችን ማሻሻል ፣የዳኝነት ነጻነትን በተግባር ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የጸጥታና የህግ አስከባሪ አካላት ለሕግ ተገዢ እና ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራት ናቸው።

የፀረ-ሽብር ህጉ በርካታ ጥቅል፣ ግልጽነት የጎደላቸውና ለአሻሚ ትርጉም የተጋለጡ አንቀጾች ያሉት ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች፣ የዜጎችን ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት የሚገድቡ፣ መንግስትን መተቸትና መቃወም እንደአሸባሪነት እንዲያስፈርጅ በር የከፈቱ እና ዜጎችን በፍርሐት የሸበቡ ናቸው። አዋጁ  የአሸባሪነት አደጋን ከመከላከል ይልቅ በተለይ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን፣ አባላትና ደጋፊዎችን፣ ጋዜጠኞችና የመብት ተሟጋቾችን ለመክሰስና ለማሸማቀቅ ጥቅም ላይ በመዋሉ፣ የፖለቲካ



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

ምህዳሩ እንዲጠብ እና ዜጎች በፍትሕ ተቋማት ላይ ያላቸው እምነት እንዲሸረሸር ማድረጉን ስመጉ ይገነዘባል።

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት አዋጅ፣ በተለይ በሰብዓዊ መብቶች፣ በጾታ፣ በሐይማኖትና በብሔር እኩልነትና መቻቻል ጉዳዮች፣ እንዲሁም በህጻናትና አካል ጉዳተኞች መብቶች ላይ የሚሠሩ የሲቪል ማሕበረሰብ ተቋማትን የገቢ ምንጭ የገደበ፣ የኢትዮጵያውያን የመደራጀት መብት መገለጫ የሆኑ ድርጅቶችን ገንዘብ ከውጭ በማግኘታቸው ብቻ እንደ ውጭ ድርጅት በመፈረጅ እና የይግባኝ መብታቸውን ጭምር የነፈገ፣ ድርጅቶችን እግር ተወርች ጠፍረው አላሰራ ያሉና ምክንያታዊነት የጎደላቸው መመሪያዎች እንዲወጡ በር የከፈተ፣ እንዲሁም ለተቆጣጣሪው የመንግስት አካል ያልተገደበ ስልጣን ከመስጠቱም በላይ ድርጅቶችን ከመደገፍና ከማበረታታት ይልቅ የመቆጣጠርና የመቅጣት አባዜ የተጠናወተው በመሆኑ ስር ነቀል ማሻሻያ ያስፈልገዋል። አዋጁ በዜጎች የመደራጀት መብት ላይ ከጣለው ኢህገመንግስታዊ ገደብ አልፎ፣ ድርጅቶቹ ህዝብን ስለመብቱ በማስተማርና ንቃተ ህሊናውን በማሳደግ፣ የሴቶችን፣ የህጻናትን፣ የአካል ጉዳተኞችና ሌሎች ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን መብት በማስከበር የሚያከናወኑትን በጎ ተግባር ጭምር እንዳይፈጽሙ መሰናክል በመሆኑ፣ ውጤቱ የዜጎች መብት መሸራረፍ ሆኗል። ዜጎች በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች በነጻነት የሚከራከሩባቸውና የሚወያዩባቸውን መድረኮች በማዘጋጀት ለዲሞክራሲያዊ ባህል ግንባታ አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ የነበሩ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት የዚህ አዋጅ ሰለባ በመሆናቸው ውጤቱ ዞሮ ዞሮ ሐገርና ሕዝብን የሚጎዳ፣ አሁን በሀገሪቱ ለምናየው አለመረጋጋትና ማባሪያ የሌለው ተቃውሞ አስተዋጽኦ ያደረገ ሆኗል። በመሆኑም የገዢው ፓርቲ፣ የሲቪል ማሕበረሰብ ተቋማት የተጣለባቸው ገደብ እንደሚነሳ በገለጸው መሠረት፣ የአዋጁን ገዳቢ አንቀጾች በአስቸኳይ በማንሳት ቁርጠኝነቱን እንዲያሳይ ይጠበቃል።

በተመሳሳይ የምርጫ ሕጉ፣ ዜጎችና የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ምርጫን ለመታዘብና የምርጫና ስነዜጋ ትምህርት ለመስጠት ያላቸው መብት በምርጫ ቦርድ መልካም ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ችሮታ እንዲሆን ያደረገ፣ ፈቃድ ለመስጠት ተገቢ ያልሆኑና ግልጽነት የጎደላቸው ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ለአደሉአዊ አሰራር በር የከፈተ፣ በጉዳዩም ለፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳይኖር በማድረግ ፍትሕ የማግኘት ሕገመንግስታዊ መብትን ያጠበበ በመሆኑ ሊሻሻል የሚገባው ነው። ከእነዚህ ሕጎች በተጨማሪ፣ በየጊዜው በሚወጡ ሕጎች የዜጎች መብቶች በገለልተኛ ፍርድ ቤት እንዲከበሩ ሳይሆን፣ በአስተዳደራዊ ይግባኝ ብቻ እንዲታዩ በማድረግ፣ የአስፈጻሚው አካል ከህግ በላይና ከፍርድ ቤቶች ቁጥጥር ውጭ ሆኖ እንዲታይ የሚያደርጉ በመሆናቸው፣ ፍርድ ቤቶችም በህግ የተሠጣቸውን የዜጎች ሰብዓዊ መብት የማስከበርና ህግ አውጪውንና አስፈጻሚ አካላትን የመቆጣጠር ስልጣን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ፣ራሳቸውን በራሳቸው እየገደቡና ተነሳሽነት እያጡ መሔዳቸው ጉዳዩን የበለጠ ውስብስብና አስቸጋሪ አድርጎታል። እነዚህ መሠረታዊ ጉዳዮች በመንግስት የማሻሻያ እርምጃዎች በቂ ትኩረት ካልተሰጣቸው፣ የገገርው ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ በመግለጫው አሳካዋለሁ ያለው ግብም ሆነ፣ እንደ ሃገር የምንመኘው ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ዕውን ሊሆን አይችልም።

በተመሳሳይ ምርጫ ቦርድ፣ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የዕንባ ጠባቂ ተቋምና ሌሎችም የዲሞክራሲ ተቋማት፣ ከገገርው ፓርቲ ተጽዕኖ ነጻ ወጥተው፣ በበቂ የሰው ሐይልና በጀት ተደራጅተው ስራቸውን በገለልተኝነትና በነፃነት እንዲያከናውኑ ማድረግ በአፋጣኝ ሊፈጸም የሚገባና ይዋል ይደር የማይባል ተግባር ነው። በተለይ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተሻለ እንቅስቃሴ ማድረጉ ሊበረታታ የሚገባው ቢሆንም፣ ይህ ተግባር ዘላቂነትና በህዝብ ዘንድም ተዓማኒነት እንዲኖረው ለማድረግ ተቋማዊ ለውጦችን በአስቸኳይ ማድረግና አመራሩም ብቃት ያለው፣ ገለልተኛና በህዝብ ዘንድ ተዓማኒነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

በግብር ከፋይ ዜጎች ገንዘብ የሚንቀሳቀሱት የሕዝብና የመንግስት ሚዲያ ተቋማት፣ ሕገ መንግስቱ እንደሚደነግገው የተለያየ ሐሳብ የሚንሸራሸርባቸው መድረኮች ከመሆን ይልቅ የገዢው ፓርቲ ርዕዮተ ዓለምና ፕሮፓጋንዳ ማስፈጸሚያ መሆናቸው፣ በአንጻሩ ከ25 ዓመት በፊት ከእነችግሩም ቢሆን በማቆጥቆጥ ላይ የነበረው ነጻ ፕሬስ ላለፉት በርካታ አመታት በደረሰበት ዕመቃ መዳከሙ ግልጽ ነው፡፡ በተመሳሳይ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ የተወሰዱ የአፈና እርምጃዎች የዲሞክራሲ ሰርዓት ግንባታውን ወደኋላ የመመለስ ውጤት እንዳስከተሉ ለአመታት ስንገልጸው የቆየነው ጉዳይ ቢሆንም፣ ገዢው ፓርቲ ከረፈደም ቢሆን እነዚህን ችግሮች መገንዘቡና ለለውጥ መዘጋጀቱ ጠቃሚ ነው፡፡

በመጨረሻም፣መንግስት ከላይ የተዘረዘሩትን ጨምሮ ሌሎችንም ስር ነቀል የሕግ፣ የፖሊሲና የአሰራር ማሻሻያዎችን በመውሰድ በሀገሪቱ ለሰላም፣ ለሰብዓዊ መብት መከበር እና ለዲሞክራሲ መስፈን ያለውን ቁርጠኝነት በተግባር እንዲያሳይ  ሰመጉ በአጽንኦት ይጠይቃል፡፡  በሀገራችን የሰብዓዊ መብት መከበር፣ ብሎም ሰላምና ዲሞክራሲን የማረጋገጥ ጉዳይ የመንግስት ብቻ ሳይሆን፣ የሐይማኖት ተቋማት፣ የሲቪል ማሕበረሰቡ፣ የመገናኛ ብዙሀንና የመላውን ሕብረተሰብ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ፣ መንግስት እነዚህ አካላት በነጻነት የሚጠበቅባቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡ እነዚህ አካላትና መላው ሕብረተሰባችንም በዚህ ረገድ አስፈላጊውን ርብርብ በማድረግ ሀገራችን ከገባችበት ቀውስ እንድትወጣ ተገቢውን ጥረት እንድናደርግ ሰመጉ አጥብቆ ያሳስባል፡፡

**ሁሉም ሰብዓዊ መብቶች ለሁሉም!**

**የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ**

**አዲስ አበባ**

ሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው፡፡
**HRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights**